ጉባዔ-ሦስት

SERMON-3

ከጉባዔ-ሁለት ለማስታወስ



አሮጌውን በር እናድስ!

## የትምህርቱ ዓላማ፤

፩ኛ-እግዚአብሔርን ማወቅ በራሱ ሕይወት ስለሆነ ለአምልኮ እንዲያግዘን፤

፪ኛ-የወልደ እግዚአብሔርን አምላክነቱን አዳኝነቱን ሰፋ አድርጎ ለማየት፤እና

፫ኛ-የቤተክርስቲያናችንን ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራዕይ ለመደገፍ፡፡



## የትምህርቱ ዓላማዎች.....በሌላ አገላለጽ

† የትምህርቱ ዓላማዎች (በዋናነት)

- የቀደመውን የእግዚአብሔርን ጥልቅ ሃሳብ መለስ ብሎ በማየት፤ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፥ ሴይጣን ዉሸተኛ ለማለት፥
- መዳናችንን በማስረገጥ ፣ የድነትን ጽንሰ ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማስረዳት፤ ከተለመደዉ ዓይነትም ወጣ ብሎ የነገረ-ድነት ማጣቀሻ ጽሑፍ ለሚማርም ፥ ለሚያስተምርም ለማቅረብ፥
- ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በቃል ስለምንሰጠው ምስክርነት ግንዛቤያችንን ለማስፋት ፥ እና
- ከዘፍጥረት 1-3 ያሉትን ዋና ሃሳቦች አጉልቶ በማሳየት ፤ የዘፍጥረት መጀመሪያው አምላክ ፣ የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስም ሁሉ አምላክ እንደሆነ በመግለፅ ላይ አነጣጥሯል።



† የትምህርቱ ዓላማዎች (ከግንዛቤ በማስገባት)፡

- ቀደም የተረዳነዉን እዉነት ለማጠናከር፥ የረሳነዉን ለማስታወስ፥ የተሳሳትነዉን ለማረም፥ ያላወቅነዉንም ለማሳወቅ ነው፤ ስለዚህ ሁላችንም ተማሪዎች ነን!
- ተናጋሪዉንና አነጋገሩን ሳይሆን የሚነገረዉን እዉነት ልክ እንደ ቤሪያ ክርስቲያኖች ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ በመመዘን ከተቻለ ሁሉንም ፥ ካልሆነ ከፊሉን መቀበል ብልህነት ሲሆን፥ ሁሉንም አለመቀበል ደግሞ የራስ መብት ነዉ።



† ትምህርቱ የቤተክርስቲያኗን መሰረታዊ አስተምሮ ፍሬም የጠበቀ ቢሆንም፤ ከሁሉ በመሻል ለማስተማር ሳይሆን፤ በመዘጋጀትም ይሁን በማቅረብ ለመማር የሚሰጥ በመሆኑ፤

- ✓ ይህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ትምህርቱን የማረም መብት አላት።
- ✓ መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ የቃላት ግድፈቶችን በማረም ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ማስገንዘቢያ

† አሮጌውን ቅጥራችን እናድስ ስንል፦

✓ እግዚአብሔር በዔድን ገነት የተናገረው ሁሉ እዉነት ነዉ፤ መነሻችንም ፥ መድረሻችንም እርሱ ነዉ። እያልን ነው።

✓ አንድም ፤ የዘፍጥረቱ እግዚአብሔር የተቀረዉ መጽሓፍ ቅዱስ ሁሉ አምላክ ነው። ከዘመን በኋላም በልጁ በኩል የተናገረው ሁሉ እውነት ነው። እያልን ነው።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

# ባለፈዉ ሳምንት

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠዉን ተስፋ ሴይጣን እንዴት ባለ ተንኮል እስራኤልን፣ አስቀድሞ ለወርቅ ጥጃች የእግዚአብሔርን ሥም ሰጥተዉ በተራራ እንዲሰግዱ ካደረገ ወዲህ፣ ወደ በዓል ጣዖት አምልኮ እንደወሰዳቸዉ ተመልክተናል፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

2.ነብየ እግዚአብሔር ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ለይ ለብቻዉ ቆሞ የበዓልን አምልኮ ካዋረደ ወዲህ፣ 12 ድንጋይ ወስዶ የፈረሰዉን የእግዚአብሔር መሰዉያ በመስራት የቀደመዉን የአብርሃም፣ ይስሃቅ፣ያዕቆብም ቃል-ኪዳን ሕዝቡ እንዲያስብ እንዳደረገ በዚህ ምሳሌም የዘመናችን ቤተክርስቲያን ወደ ዕለተ ጰራቂሊጦሱ ትምህርት ዘወር ማለት እንዳለባት አስታዉሰናል፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባህርይም ተመልክተን፤ ከዚሁ አስተምሮ መሰረተ ሃሳብ አኳያ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ወይም ክርስቶስን መቀበል ማለት በራሱ ምን ማለት ነዉ??? ብለን ጠይቀን

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

መልሱን፦ ከአዳም የተላለፈብኝን ኃጢአት ያስወግድ ዘንድ፥ ከብፅዕት፥ንጽሕት፥ ድንግል ማሪያም ያለ አባት ተወልዶ ፥ በሥጋ የተገለጠዉ ኢየሱስ፤ እርሱ የእግዚአብሔር መልክ ያለዉ፤ ራሱም እግዚአብሔር የሆነ፥ የክብሩ መንጸባረቅ ነዉ። ከሁሉም በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ የሆነው እርሱ ፤ ወደ እግዚአብሔር የምቀርብበት ብቸኛ መንገዴ ነዉ። ብሎ ማመን ነዉ። በማለት መልሰን ነበር፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

እንዲሁ. . . .እግዚአብሔር ህለወቱን በፍጥረትም በመጽሐፍ ቅዱስም ገልጧል የሚለዉን ሃሳብ ገልጠን ተናግረን፤ ከዚህ አስተምሮ መሰረተ ሃሳብ አኳያ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመን ወይም ክርስቶስን መቀበል ማለት በራሱ ምን ማለት ነዉ??? ብለን ብመጠየቅ

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

መልሱን፦ ጌታ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጥረታት ፈጣሪና የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ማዕከል ነዉ። የእግዚአብሔርን ክብር የሚናገሩት ሰማያት የእጁ ሥራ ናቸዉ። እርሱም የመጽሐፍ ቅዱስ ቋሚ አምድ ነዉ። የኔም ሕይወት አምድ ነዉ።ብሎ ማመን ነዉ። በማለት መልሰን ነበር፡፡

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

እንግዲህ...አሮጌዉን በር እናድስ ስንልም እግዚአብሔር ለሰዉ ልጅ በሚገባዉ ቃል-ኪዳን መጀመሪያ ላይ የሚሰጠዉ መመሪያ የቃል-ኪዳኑ መሰረት ስለሆነና፣ ሴይጣንም ዓላማዉ ይህን መሰረት መናድ ነዉና፣ የቀደመዉን የእግዚአብሔር መመሪያዎች እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅዶቹ እንያዛቸዉ እያልን ነዉ።

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ይህንኑ ሃሳብ በምሳሌ ለማስየት፣

- እግዚአብሔር ለአብርሃም በስጠው ተስፋ መሰረት እስራኤልን ከግብፅ በበረታ ክንድ በኩር ገድሎ፣ ባሕር ከፍሎ፣ ከዓለት አፍልቆ በማጠጣት፣ መና አዉርዶ በማብላት 40 ዓመታት በሙሉ መርቱአቸዋል፣
- ሰዉነታችን ይህንን ቀላል እንጀራ ተጠየፍ ብለዉ ባጉረመረሙ ጊዜ ግን እግዚአብሔር እባብ አስነስቶ በማስፈደፉ ከሕዝቡ ብዙዎች ሞተዋል፣
- ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያየት በሕይወት ይኖራል አለው። ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ። [ዘኁ21[8-9]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ይህንኑ ሃሳብ በምሳሌ ለማስየት፣

- እግዚአብሔር አንዲያ ልጁ እዉነትኛ እንጀራ ነዉና ፡-የዚሁ ምሳሌ የሆነውን ከሰማይ አዉርዶ ያበላቸዉን መና፣ ስለሰዉ ዘር በሙሉ የተሰቀለዉን ስቅለቱንም ያዩ ሁሉ አምነዉ የሚድኑበት ምሳሌ የሆነዉን ና እስራኤል በእባብ በተነደፉ ሙሴ በዓላማ ለይ የሰቀለውን የናሱን እባብ ፣ ለትውልድ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ድንኳኑ ዉስጥ እንዲቀመጡ ሆነዋል። [ዮሃ3[15]]

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ይህንኑ ሃሳብ በምሳሌ ለማስየት፣

- በሚያስግርም መልኩ የእስራኤልም ልጆች እስከ እርሱ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሕዝቅያስ ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረዉ።[2ነገ18[4]]

....አስደናቂ ሚስጢር ያለበትን የናሱን እባብ ሲያስግድ እንደነበር ልብ ይሉታል!

መሰረታዊ አስተምሮዉን ባልቀየረ መልኩ ይህንን ትምህርት በማንኛዉም ዓይነት መንገድ ለሌላዉ በማዳረስ በአገልግሎቱ ይሳተፉ።

ይህንኑ ሃሳብ በምሳሌ ለማስየት፣

- አሁንም በሚያስግርም መልኩ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች መና አዉርዶ የማብላቱ እዉነት ደብዝዞ፣ ጌታ በነበረበት ዘመን ሙሴ መና እንዳወረደ እስከመታመን ደርሶ እንድነበር ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ [ዩሃ6፡32] ብሎ ከመለሰዉ መልስ እንረዳለን፡፡



ዛሬም በቤተክርስቲያን መጀመሪያቸዉ መልካም የነበረዉን የሥዕልና የመስቀልና አጠቃቀም፣ የጌታ ዕለት አከባበር ወዘተ መልካቸዉን ቀይረዉ ስግደትና ዉዳሴም ይዘዉ ማየታችን የዚሁ ሌላዉ ነፀብራቅ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

በዚሁ አይነት ታናሽነታችንን ሳንዘነጋ፣ ትምህርታችንን አሮጌዉ በር ያልንበት መሰረታዊዉ ዓላማም፣ ወደቀደመዉ የእግዚአብሔር አጀንዳ፣ ወደ መጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያንም ፅንሰ ሃሳብ እንመለስ የሚለዉን አጉልቶ ለማሳየት ነዉ፡፡

እግዚአብሔር አጀንዳዉን ሳይቀይር ሰዉን ብቻ ቀይሮታልና፡፡ በዚሁ አሮጌዉን በር እናድስ ስንል እግዚአብሔር ለሰዉ ልጅ በዔድን ገነት የተናገረዉ ሁሉ እዉነት ነዉ እያልን ነዉ።